July 7, 2009 Institute of Development and Education for Africa (IDEA)

# ማን ነው ኢትዮጵያዊ?

## ዶ/ር ገላውዴዎስ አርኣያ

ይኸንን ጽሑፍ ለማበርከት የፈለግኩበት ዋና ምክንያት፡ አሁን በገጠመን የቀውጢ ቀን፡ ኢትዮጵያውነት በተመለከተ ከየቦታው በተዛባ መልኩ ሲቀርብ ስለታዘብኩና ስልከነከነኝም ጭምር ነው። የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውነት ጽንሰ ሐሳቦች ምንጫቸውና አመጣጣቸው በመጠኑ ካቀረብኩ በኋላ፡ ፖለቲካዊና ኅብረተሰባዊ አገላለጻቸው ደግሞ፡ አጠቃላይ የአገራችን የታሪክ ሂደት መሠረት በማድረግ ሰፋ ባለ መልኩ ለመተንተን እሞክራለሁ።

የ 'ኢትዮጵያ' ጽንሰ ሐሳብ ስርወ ወይም መሰረታዊ አመጣጥ ከጥንታዊ የግሪክ ቋንቋ 'ኢትዮኦፕስ' (ethio-ops) ከሚል ቃል የመነጨ ነው፣ ቀጥተኛ ትርጉሙ ደግሞ (በፀሐይ) የተቃጠለ ፊት ማለት ሲሆን፡ በስነ-ጽሑፍ አጠቃቀሙ ግን 'ጥቍር' ወይም 'ጠይም' ማለት ነው። የጥንት ግሪኮች ታድያ ኢትዮጵያ ሲሉ ጠቅላላ አፍሪቃን ማለታቸው ሲሆን፡ 'ኢትዮጵያዊ' ደግሞ ለማንም ጥቍር ሕዝብ የሰጡት መለዮ ወይም ማንነት ስለነበር በነሱ ቤት ሁሉም አፍሪቃዊ ኢትዮጵያዊ ነበር። በአምስተኛው ምእተ ዓመት ዓመተ ዓለም አጋማሽ ላይ ዝነኛው ግሪካዊ የታሪክ ተመራማሪ፣ እንድያውም የታሪክ አባት ተብሎ የተነገረለት፣ ሄሮዶተስ ግን 'ኢትዮጵያ' ወይም 'ኢትዮጵያዊ' በቀይ ባሕር ዳርቻ ለሚገኝ ሃገር (ያሁኗ ኢትዮጵያ) እና ሕዝብ (የአሁኑ ኢትዮጵያውያን ቅድመ አያቶች) መሆናቸውን ለይቶ በማስቀመጥ በተለያዩ ጽሑፎቹ ዘግቦታል።

በሰፊው የ 'ኢትዮጵያ' ጽንሰ ሐሳብ በመንተራስ መጠነኛ ጥናትና ምርምር ብናደርግ ደግሞ የምናገኘው ሐቅ ቢኖር እስከ አ17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ጠቅላላ አፍሪቃ ኢትዮጵያ ተብሎ ነበር የሚታወቀው፣ የአሁኑ አትላንቲክ ውቅያኖስ ደግሞ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ነበር ስሙ። በአናሳ ወይም ጠባብ ፍቺ 'ኢትዮጵያ' የሚል ቃል ከተጠቀምን በእርግጥ የአሁንዋ አገራችን ለመሆኗ የሚያጠራጥር ባይሆንም፣ ይህች አገር ከፍተኛ የጥንት ስልጣኔ ስለነበራት፣ ከስልጣኔም ጋር የማስፋፋት ዝንባሌ፡ ብሎም የሕዝቦች ቅይጥነት ሰለሚያስከትል፣ በሦስተኛው ምእተ ዓመት ዓመተ ምሕረት (270 ገደማ) የአክሱም ንጉስ አፌላስ ቀይ በሕር ተሻግሮ ሒጃዝን (አሁን ሳውዲ ዓረብያ ውስጥ) ተቆጣጥሮ ስለነበር፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት በዛን ጊዜ በሕጃዝና ዙርያ ከሚገኘው ሕዝብ ተቆራኝቶ ስለነበር፡ አሁን በደቡብ ሳውዲ ዓረብና የመን አከባቢ ሓበሻን የሚመስል ሕዝብ ማየቱ የሚያስደንቅ አይሆንም። ይህ የታሪክ ክስተት ለሁለተኛ ጊዜ በአጼ ኤዛና፣ ለሦስተኛ ጊዜ ደግሞ በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግስት ተተግብሯል።

በአራተኛው ምእተ ዓመት ዓመተ ምሕረት አጋማሽ ላይ (330 ገደማ) የኢትዮጵያ ሠራዊት ኩሽ ወይም ኑብያን ተቆጣጥሮ ስለነበር፡ የአሁኑ የኑብያ ተወላጆች በሚያሳስት ሁኔታ ኢትዮጵያውያንን ነው የሚመስሉት። በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት (ከ 517 ዓ.ም. በኋላ) እንደገና ኢትዮጵያ ደቡብ ዓረብን ለአያሌ ዓመታት ትገዛ ስለነበር፡ የደቡብ ዓረብ ሕዝብ (ከዛም አልፎ አንዳንድ የኩወይትና የተባበሩት ዓረብ ኢሚሬት ሕዝቦች) ከኢትዮጵያውያን ጋር በመልክ መመሳሰላቸው፡ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው የታሪክ ሐቅነት ጋር የተያያዘ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

የተለያዩ ሕዝቦች ግንኙነት ግን በጦርነትና መንግሥት-ስፋትነት ብቻ ሳይሆን በሕዝብ መፍለስ፡ በንግድና በጋብቻም ጭምር የሚፈጸም ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመክሮም ከዚሁ ታሪካዊ ሂደት ማምለጥ ስለማይችል ለብዙ ሺ ዘመናት በሰለማዊና ኢሰላማዊ መንገዶች ዝምድናዎችን ሲፈጥር ስለቆየ፡ ኢትዮጵያ ኅብረ-ቢሔር ለመሆኗ የሚገርመን አይሆንም። እንደ ያውም፡ ሓበሻ ማለት ቅይጥ ሕዝብ ማለት ነው። ነገር ግን ቆየት ብለን እንደምናየው ሁሉ "ሐበሻ" የኢትዮጵያውያን ሁሉ ስያሜ አይደለም።

የአንድ ሕዝብ ቅይጥነት፡ በባህልና ቋንቋ መመሳሰል እና የጋራ ስሞችን መጠቀም ወዘተ ሊንጸባረቅ ይችላል። እነዚህ ሕዝቦች ታድያ በጎሳ፡ ብሔረሰብ፡ ብሔር ወዘተ ራሳቸውን ቢገልጹም ቅሉ የላቀና የጋራ ማንነታቸው ግን አገር-አቀፍ የሆነውን ኢትዮጵያዊ የሚለውን መለዮ ነው። ለምሳሌ፡ የሰዎች ስም ብንወስድ በርሃነ (ትግርኛ)፡ ብርሃኔ (አማርኛ)፣ ተስፋይ (ትግርኛ)፡ ተስፋዬ (አማርኛ)፣ አስፍሃ (ትግርኛ)፡ አሰፋ (አማርኛ) ትርጉማቸውና አደማመጣቸው አንድ ነው፣ የሁለቱ ቋንቋዎች መሰረት ደግሞ ግእዝ ነው። ነገር ግን 'ደስታ ገብረወልድ' እና 'ህይወት ገብረማርያም' የጎጥ ወይም ጎሳ ማንነታቸው ካልገለጹ በስተቀረ የብዙ ኢትዮጵያውያን የጋራ ስሞች (በተለይም የትግራይ፡ አማራና ጉራጌ ብሔር ተወላጆች) ስለሆኑ ሃገራዊና አድማሳዊ ባህልን ነው የሚያንጸባርቁት።

የቦታ፡ የሰፈር፡ ወይም የመንደር ስሞች ከወሰድን ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ባህልና ማንነትን የሚያንጸባርቁ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ ቦረና፡ ጨርጨር፡ ውጫሌ ወዘተ በደቡብ፡ ምስራቅና መሃል-ሰሜን ኢትዮጵያ መገኘታቸው የአንድን ሕዝብ እንቅስቃሴ ወይም ፍልሰት መኖሩን ያሳየናል። የዚሁ ዓይነተኛ ምሳሌና በመጽሐፌ በ <u>መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች</u> እንደጠቀስኩት ሁሉ የ16ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ የኦሮሞ ተወላጆች ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ መሃልና ሰሜን ኢትዮጵያ መጓዛቸውን ነው የሚያሳየን። ሌላ ከዚሁ ጋር የተያያዘና በመጽሐፉ የጠቀስኩት ነገር ቢኖር በትግራይና በኤርትራ ወስጥ አንድ ዓይነት የቦታና የመንደር ስሞች መኖራቸው ነው። ለምሳሌ 'ሰሓርቲ' መቐለ አከባቢ አለ፡ 'ላምዛ ሰሓርቲ' ሓማሴን ውስጥ አለ፣ 'አስገደ' ሽረ ውስጥ አለ፡ 'ቤት አስገዳ' ኤርትራ ውስጥ አለ፣ 'ዓዲ አቤቶ' ዓድዋ አከባቢ አለ፡ 'ዓዲ አቤቶ' የሚባል መንደር ከአስመራ በስተምዕራብ አለ፣ 'ማይልሓም' ጎንደር፡ ትግራይና ኤርትራ ውስጥ ይገኛሉ።

አቶ በላይ ግደይ <u>አክሱም</u> በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ 'መንዝ' 'መንዩ'ዚ' (ማን ነው ይኸ?) ከሚል የትግርኛ ቃል የፈለቀ መሆኑን ጠቅሰውታል። እንደዚሁም፡

‘ቀብሪ ደሓር’ የተሰኘውን በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኘውን የመንደር-ከተማ ስም እንዳለ ትግርኛ ሆኖ፡ ትርጉሙ ደግሞ ‘ቀብር በኋላ’ ነው።

ሰፋ ያሉ የህዝቦች ሕብረተሰባዊ፡ ታሪካዊና፡ ፖለቲካዊ ጥናት ካደረግን ደግሞ የኋላኋላ እንኳንስ በኢትዮጵያ ያሉ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች፡ በጠቅላላ የአፍሪቃ ቀንድ፡ ሰሜን ሱዳንና ደቡብ ዓረብ የሚገኙ ሕዝቦችም ጭምር በብዙ ረገድ የተቆራኙ መሆናቸውን እንገነዘባለን። በኢትዮጵያ ውስጥ የሱማሌ ብሔር ስላለ ኢትዮጵያና ሶማልያ ፡በጥላቻም ይሁን በወዳጅነት፡ ምንጊዜም ዝምድና ይኖራቸዋል፣ ይህ ዝምድናም አወንታዊ ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ ግን መጀመርያ ሰላምና መረጋጋትን መስፈን አለባቸው። የሰፊው የኦሮሞ ሕዝባችን ዘመዳሞች የሆኑት ቦራን፡ ሳኩየ እና ጋባራ የተባሉት አሮሞዎች ከንያ ውስጥ ስለሚገኙ በነሱ አማካኝነት ኢትዮጵያና ከንያ መልካም ግኑኝነትና ጉርብትና ሊኖራቸው ይችላል። አኘዋክና ንወር ደግሞ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና ደቡብ ምስራቅ ሱዳን በኩታገጠሙ አዋሳኝ ላይ ስለሚገኙ በሁለቱ አገሮች የሰላምና የመተባበር ድልድይ እንዲኖር ማበርከት ይችላሉ። የትግራይ ሕዝብ እንደዚሁ በኢትዮጵያና በኤርትራ የወደፊት ግንኙነቶችን አስመልክቶ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል።

ከላይ እንዳየነው እንግዲህ የልዩ ልዩ ሕዝቦችና አገሮች ግንኙነቶች የተወሳሰበና የተጥለፈለፈ ነው፣ ለዘመናትም አብሮው ጎን ለጎን ቢኖሩም ቅሉ አልፎ አልፎ ግን በ ጠብ-መንጃ ተፈላልገዋል። በዙውን ጊዜ፡ የጠቡ መንሻ፡ 1) ሰፊው ሕዝብ ከፍ ብሎው የተጠቀሱትን ታሪካዊ ሓቆችን ባለመገንዘብ፣ 2) ልዩ ልዩ በሥልጣን ላይ የተቆናጠጡ መንግስታት ከፋፈለው ለመግዛት ይቻላቸው ዘንድ ሕዝቡን ስላናቆሩት ነው።

አሁን ትኵረቱ ወደ ኢትዮጵያ በማድረግ፡ ማን ነው ኢትዮጵያዊ? የሚለውን ጥያቄ ልመልስና የወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ከጥያቄው ጋር በማገናዘብ ለመተንተን እሞክራለሁ። ብቃት ያለውና ስኬታማ ትንታኔ እንዲሆን ከተፈለገ ግን፡ 1) በሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ መንግስት አስተዋጽኦ፡ 2) የተቃዋሚ ኃይሎች የፖለቲካ አጀንዳዎችና አደረጃጀት፡ 3) የምሁራንና ሊሂቃን ታሪካዊ ኃላፊነትና ሚና በዝርዝር ማቅረቡ አስፈላጊ ይሆናል።

ትንተናው ከማቅረቤ በፊት ግን ማን ነው ኢትዮጵያዊ የሚለውን ጥያቄ ልመልስ። ከትግራይ እስከ ሞያሌ፣ ከመተማ እስከ ሱማሌ ድንበር፣ ከግምቢ እስከ ጂቡቲ ድንበር ያለው ሕዝብ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ነው። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን “ኢትዮጵያ የሚለው አገላለጽ ኤርትራም ማከታት አለበት፡ ምክንያቱም የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነው” የሚሉ አሉ። ይህ አመለካከት በከፊል እውነትነት ያዘለ ቢሆንም የኤርትራውያን ስነ-ልቦናና ስሜት በቅጡ ስለማይገነዘብ ግን ሙሉ በሙሉ ርትዓዊ ነው ማለት አይቻልም። በእርግጥ የኤርትራ ሕዝብ በታሪክ፡ በባህል፡ በኃይማኖት፡ በቋንቋ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የተሳሳረ ነው። ትግርኛ፡ ሳሆ፡ አፋር፡ ኩናማ በኢትዮጵያና በኤርትራ ኩታገጠም ድንበር የሚነገሩ ቋንቋዎች ናቸው። በምስራቅና ሰሜን ኤርትራ የሚነገረው ትግሬ የተባለው ቋንቋ ደግሞ ከትግርኛ እና አማርኛ በይበልጥ ከግእዝ የመነጨ ለመሆኑ አያጠራጥርም። ይሁንና፡ ያሁኑ የኤርትራ

ትውልድ ኢትዮጵያውያን ነን አይልም፣ በተለይም ትግርኛ ተናጋሪው ኤርትራዊ ሓበሻ ነኝ ኢትዮጵያዊ ግን አይደለሁም ነው የሚለው፣ ኦሮሞዎች በአንጻሩ ኢትዮጵያውያን ነን፡ ሐበሻ ግን አይደለንም ነው የሚሉት። የሁለቱ አመለካከት በመጠኑም ቢሆን እውነትነት ያለው ነው። የአሁኑ የኤርትራ ትውልድ አባቶች በኢትዮጵያውነታቸው ያምኑ ስለነበር 'ኢትዮጵያ ወይ ሞት' የሚል መፈክር አንግበው ታግለው ነበር። አሁን ግን እንደዛ ዓይነት ስሜትና አመለካከት ስለሌላ የኤርትራ ጉዳይ ለግዜው ትተን ዶ/ር ዳንኤል ክንዴ እና ዶ/ር ተስፋጽዮን መድሃኔ ለጀመሩት የሁለቱ ሕዝብ የማቀራረብ ውይይት መደገፍና መቀጠል የሚበጅ ይመስለኛል።

አንድ ህንጻ በሲሚንቶ፡ ጡብ፡ ድንጋይ፡ እንጨትና ሌሎች ደጋፊ ቍሳቍሶች እንደሚታነጽ ሁሉ፡ ኢትዮጵያም በልዩ ልዩ ብሔረሰቦችና ብሔሮች የተገነባች ሃገር ናት። ባሁኑ ጊዜ ግን ኢትዮጵያውነትና የኢትዮጵያ አንድነት በከፍተኛ አደጋ ስለሚገኝ ከላይ የጠቀስኳቸውን ርእሰነገሮችን በዝርዝር ማቅረብ ግዴታ ይሆናል።

1. ኢህአዴግ፡ ኢትዮጵያውነትና የኢትዮጵያ አንድነት፦ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሥነ-መንግስትና ፍትኀ-ብሔር በመፍጠር እንደ ሃገር ስትራመድ የቆየች አሃዳዊ የፖለቲካ አካል እንጂ የተወናበዱ ግለሰቦች እንደሚሉት የመቶ ዓመት ታሪክ ብቻ ያላት አገር አይደለችም። በወያኔ የሚመራው የህአዴግ መንግስት ሥልጣን ከጨበጠ ወዲህ ግን ባለስልጣናቱ ኢትዮጵያን የሚያሳንስና የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያንቋሽሽ መርሕ ስለተከተሉ የኢትዮጵያ ልዑላዊነትና የሕዝቡ አንድነትን የሚጻረሩ የፖለቲካ ክስተቶችም ተፈጥሯል። ከዚሁ ከህአዴግ ፖሊሲ አንዱ ኢትዮጵያን በቋንቋ የሚከፋፍል ክልሎችን በመፍጠሩ ነው። እኔ በመሰረቱ የፌደረሽን ስርዓትና አወቃቀር የምደግፈው እንጂ የምቃወሞው አይደለም። በልዩ ልዩ ራስገዞች የሚገኙ ብሔረሰቦችና ብሔራት ባህላቸውና ቋንቋቸውን የሚያዳቡርበት ሁኔታ ቢፈጠር የምደግፈው ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ ክልል ግን ግንኙነት እንዳይኖሮው ማድረግና የአንዱ ክልል ተወላጆች በሌሎች ክልሎች ኢንቨስትመንት የማይፈጥሩበት ሁኔታ መፍጠር፣ ከዝያም አልፎ ተርፎ በመስርያው ቋንቋ ሳይሆን በክልሉ ቋንቋ ብቻ መጠቀም (ለምሳሌ፡ ኦረምያ አከባቢ የሚታየው አዝማምያ) የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትን የሚንዱ ናቸው።

   ድሮ የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ የሞያ ማሕበራት የተደራጁት በብሔር ሳይሆን ኢትዮጵያ አቀፍ ስለነበሩ አባልነታቸውም በዛው መጠን መላ ኢትዮጵያን የሚያንጸባርቁ ነበሩ። ለምሳሌ፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማሕበር፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ወዘተ። አሁን ኢትዮጵያ አቀፍን የሚጻረሩ የክልል ማሕበራት ስለተፈጠሩ፡ ልዩ ልዩ ብሔራትን ያቀፉ ማሕበራት ቀስ በቀስ የሚጠፉበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ይህ ዕጣ በኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር ለመድረሱ ሁላችን የምናውቀው ሓቅ ነው።

በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት የሕዝቡ በመልክዓ ምድር መነጣጠል ብቻ ሳይሆን፡ የክልሎቹ የመገንጠል መብትም (አንቀጽ 39) በሕገ መንግሥቱ መስፈሩ ነው። ይህ ድንጋጌ የሃገር አንድነት የሚጻረር ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያዊ ነኝ ለሚለው ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ የጋራ ማንነትህ አብቅቷል፣ አዲሱ መለዮህ ትግራይ፡ ኦሮሞ፡ አማራ፡ አፋር፡ ሲዳማ ወዘተ ነህ ብሎ እንደማለት ነው።

ሌላ በጣም አስፈሪ ክስተት የተፈጠረው ቢኖር ደግሞ በኢህአዴግ ዘመን አልፎ አልፎ የብሔርና ኃይማኖት ግጭቶች መካሄዳቸው ነው። እነዚህ ግጭቶች ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ ባለሥልጣናት የተቃኙና የታቀዱ ናቸው ብሎ ማቅረብ፣ በተለይም ተጨባጭ መረጃ በሌለበት፣ ርቱዓዊነት የተከተለ ማጠቃለያ ሊሆን አይችልም። ነገር ግን ቀደም ብሎ በሃረር አከባቢ የተደረጉ ግጭቶች፣ ከአንዴም ሁለቴም በኦሮሞና አማራ ተወላጆች ወለጋ አከባቢ የተካሄዱ የጥላቻ ግጭቶች፣ በአሶሳ የተካሄደው የሕዝብ እልቂት፣ በደቡብ ኢትዮጵያ በሰይፍ የተገደሉ የኢትዮጵያ ተወህዶ ቤተክርስትያን ከህናት፣ አልፎ አልፎ በአዲስ አበባ የቦምብ ፍንዳታዎች (ትግራይ ሆቴል፣ ላሊበላ ሆቴል፣ በሕዝብ ግልጋሎት/ታክሲ)፣ የእስላምና ክርስትያን ግጭቶች በማርካቶና ደሴ። እንዲህ ዓይነት ግጭቶች ከዚህ ቀደም አልነበሩም። ወንጀለኞቹ በህቡእ ስለሚንቀሳቀሱ ደግሞ በኃላፊነት የሚጠየቅ ግለሰብ ወይም ስብስብ ሊኖር አይችልም። ነገር ግን፡ በማንኛውም ረገድ የመጀመርያው የመንግሥት ሓላፊነት ሰላምና መረጋጋትን መጠበቅ ስለሆነ፡ የኢህአዴግ መንግሥት በሕዝብና በታሪክ ፊት ይጠየቃል።

2. የተቃዋሚ ኃይሎች የፖለቲካ አጀንዳዎችና አደረጃጀት፦ በሃገር ውስጥም በውጭም ያሉት ተቃዋሚ ኢትዮጵያውያን ወይ በብሔር ወይም ደግሞ በሃገር-አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው ነው የሚንቀሳቅሱት። ሁሉም ግን ኢትዮጵያውያን ነን ነው የሚሉት፣ አጠቃላይ የኢትዮጵያ አጀንዳ ያላቸውም ይመስላል፣ የጋራ መፈክራቸውም 'የኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት' ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አንዳንድ ተቃዋሚ ስብስቦች ራሳቸውን በላቀ ደረጃ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን በተለያየ መልክ ከመግለጻቸወም በላይ፡ የሌሎች ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያወነት ግን እንደሚጠራጠሩት ነው የሚያስቀምጡት። ይህ አመለካከት አዲስ ባይሆንም፡ ጎልቶ መታየት የጀመረው ግን ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኃላና፡ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት የቋንቋ ክልሎችን ከፈጠረ በኃላ ነው። ይሁንና ተቃዋሚ ኃይሎች የተባሉት ግን ለምን የጎጥ ፖለቲካ እንደመረጡና 'ኢትዮጵያ' በሚል ሽፋን ተደራጅተው መንቀሳቀስ እንደፈለጉ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ነው። እነዚህ ጠባብ አመለካከት ያላቸው ስብስቦች በሁለት ነው የሚከፈሉት፦ ሀ) በስታር ባክስ ቡና ቤቶች፡ በኢትዮጵያ ምግብ ቤቶች እና በዕለተ ሰንበት በየቤተክርስትያኑ በመሰብሰብ ወሬና አሉባልታ ሲነዙ የሚውሉ ናቸው። የነዚሁ የባከኑ የኢትዮጵያውያን ስብስቦች የ "ዜናና ሓተታ" ምንጮች ደግሞ በግለሰቦችና በድርጅቶች ባለቤትነትና ስራ አስከያጅነት የሚስተዳድሩ የሬድዮ አገልግሎቶች ናቸው፣ የጋራ ጠላታቸው "ወያኔ" ሆኖ በትግራይ ሕዝብና በገዢው ፓርቲ ያለው ልዩነት ግን ፈጽመው ማየት አልቻሉም

ወይም ለማየት አልፈለጉም። በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጥያቄ ቢኖር "ወያኔ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ ያቀደ ድርጅት ነው፡ የኢትዮጵያ ሃብት በሙሉ ተነቅሎ ወደ ትግራይ እየሄደ ነው" ወዘተ የሚሉት ነው። የተወናበደ ስብስብ መሠረት የሌለው ወሬ ብያናጋ ግን የሚያስደንቅ አይሆንም። ለ) በሲቪክ ማሕበራትና ፖለቲካ ድርጅቶች ዙርያ የተደራጁ ስብስቦች ሆኖው አንድአንድ ምሁራንና ሞያተኞች ውስጠ ደንብና የፖለቲካ ፕሮግራም በማርቀቅ አንጻራዊ የፖለቲካ ራእይ እንድያራምዱ ይረዷቸዋል። ከ 'ሀ' ስብስብ በብስለታቸውና አመለካከታቸው እጅግ በጣም ቢለዩም፡ በድርጅት ቅልቅልነታቸውና አጠቃላይ ስሜታቸው ግን ብዙ አይለዩም። እነሱም ቢሆኑ 'ኢትዮጵያ' የሚል ስም ይያዙ እንጂ የጎጥ ፖለቲካ ከማራመድ አልተቆጠቡም። የ 'ሀ' ስብስብ በግልጽና በይፋ "ወያኔና ወያኔዎች ጠላቶቻችን ናቸው" ሲሉ፡ የ 'ለ' ስብስብ ግን በይፋ ሳይሆን በሚስጢር "እገሌና እገሌ ወያኔዎች ናቸው፡ ስለሆነም በስብሰባችን ላይ እንዳይሳተፉ መደረግ አለበት" በማለት ወሬ የሚያናፍሱ መንፈሰ-ደካማ ስብስቦች ናቸው። ስለሆነም በችሎታና ዓይነት ከ 'ሀ' ስብስብ ይለዩ እንጂ በመንፈሳቸውና ስሜታቸው የጋራ አጀንዳ እንዳላቸው አንድም ሁለትም የለውም።

የሁለቱ ስብስቦች ዋና ዓላማ አንድ የጋራ ጠላት መፍጠር ስለሆነ ወይ በማወቅ (የ 'ለ' ስበስብ) ወይም ባለማወቅ (የ 'ሀ' ስብስብ) 'ወያኔ/ትግራይ' ትኵረታቸውና ዓላማቸው ሁኗል። የዚሁ የፖለቲካ ክስረት ዓይነተኛ ምሳሌ በ ብ/ጄነራል ኃይሌ መለሰ የቀረበውን ጽሑፍ ሆኖ፡ ጄነራሉ በቅርቡ ወደ ትግራይ ተጕዘው ያጠናቀሩት ጥናትና ዘገባ ይመስል በሚከተለው መልክ አቅርበውታል፦ "በወታደራዊ መስክ የአገሪቱ የመሳርያና የጥይት ፋብሪካዎች ተነቅለው ተወስደው ትግራይ ውስጥ ተተክለዋል። ተዋጊ ጀቶችም ከነመሳርያቸው ተወስደው ወታደራዊ መሬት ይዘው እንዲቀመጡ ተደርገዋል። የትግራይ ሕዝብ ወደፊት ሊገጥመው ለሚችል ምናልባታዊ ጦርነት በምግብ እህል፣ በልብስ፣ በመገናኛ በሕክምና አገልግሎት ወዘተ እንዳይቸገር እነዚህን ፍጆታዎች የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በአከባቢው ከማቋቋማቸው በተጨማሪ ኢፈርት በተባለው የመዝረፍያ ድርጅታቸው አማካይነት ከማህል አገር እያግበሰበሱ ወስደው አከማችተዋል። በአጭሩ በአሁኑ ወቅት በትግራይ በክምችት ያልተሞላ መጋዘን ነተራና ዋሻ የለም ማለት ይቻላል።"[1]

ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ስብስቦች ባሻገር እንደ ሦስተኛ ግንባር መታየት ያለበት በልዩ ልዩ ፓርቲዎች የተደራጁ፣ በሲቪክ ማሕበራት የተደራጁ፣ አገር-አቀፍ አስተባባሪ ድርጅት ያቋቋሙ፣ ከአልቧልታና ወሬ የራቁ፣ የኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት የሚያስከብሩና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠበቃ ሆነው የሚታገሉ፣ ሰፋ ያለ የፖለቲካና የምጣኔ ሃብታዊ ፕሮግራም ያላቸው፣ ተቃዋሚ ኃይሎችን በማቀራረብ የጋራ ራእይ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ናቸው። የኢትዮጵያ መጻኢ (የወደፊት) ብሩህ ዕድል የሚወሰነው ደግሞ በነዚህ ኃይሎች ነው። ለነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያውያን በሙሉ ያለንዳች ልዩነት ኢትዮጵያውያን ናቸው፣ በነሱ ቤት የኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያውነት አይጠየቅም፣ የብሔር ማንነትና መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድን ብሔር

ተወላጅ ግን በኢትዮጵያውነቱ እንጂ በብሔር ማንነቱን አይገልጹትም፣ አይጠሩትም።

በሃገር ውስጥ የተደራጁት ድርጅቶችም በአንዳንድ የፖለቲካ መስመሮች ላይ ልዩነት ይኑራቸው እንጂ በጋራ የኢትዮጵያ አጀንዳ የሚስማሙ ይመስላል። አንድነት (ቅንጅት) ፓርቲን የሚመሩ ግለሰቦች፡ አባሎቻቸውና ፕሮግራማቸው ጠቅላላ ኢትዮጵያ የሚያካትት ሆኖ ቅልቅሉ ግን (የኢትዮጵያ የወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ በፈጠረው ችግር ምክንያት) መላ ኢትዮጵያን የሚያንጸባርቅ አይደለም። ነገር ግን ፓርቲው ቢያንስ ቢያንስ አባልነት ለሁሉ ኢትዮጵያዊ ክፍት ማድረጉ ግልጽ ነው። በነገራችን ላይ የድሮ የኢህአፓ ዓይነት ቅልቅል ባሁኑ ጊዜ ማግኘቱ አዳጋች ሳይሆን አይቀርም።

በአንጻሩ በ መድረክ ዙርያ የተደራጁት እንደ ዓረና ትግራይና ኦሮሞ ፌደራሊስት የመሳሰሉት በፖለቲካ ፕሮግራማቸውና አወቃቀራቸው የግል ብሔሮችን የሚያስተናግዱ ሆኖው፡ የኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት ግን የሚደግፉ እንጂ የሚቃወሙ አይደሉም። በመድረክ ዙርያ ያሉት ግለሰብ የአመራር አባላት ሰፊው አባልና ደጋፊ በኢትዮጵያውነቱና ለኢትዮጵያ መጻኢ አወንታዊ አስተዋጽኦ፡ ከላይ ከተጠቀሱት የ 'ሀ' ና 'ለ' ስብስቦች ሲነጻጸር እጅግ የላቀ ነው። ይህ የኔ ብቸኛ አመለካከት አይደለም፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ በተለይም በሦስተኛው ግንባር የሚንቀሳቀሱትና አገር ቤት ካሉት ተቃዋሚ ኃይሎችም ጭምር የሚከራከሩለት ነው። አቶ አምሃ ዳኘ ባቀረቡት ጥናታዊና የበሰለ ጽሑፍ እንዲህ ይላሉ፦ "ፖለቲካቸውን በክልል ብሄርተኝነት ዙርያ ያደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ አንድነት እና ልዓላዊነት መከበርን በተመለከተ አጠራጣሪ አቋም እንደሌላቸው ይህ ጸሐፊ ይገነዘባል። በክልል ብሄረተኝነት ዙርያ መደራጀታቸው በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ዙርያ ከተደራጁት ያነሰ ኢትዮጵያዊ እንደማያደርጋቸው ያምናል።"[2]

ምናልባት ከነዚህ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ለየት ያለ አቋም ያለውና ከኢትዮጵያ አጀንዳ አፈንግጦ የሚገኘው ኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦነግ) ሳይሆን አይቀርም። ብዙ የኦነግ ደጋፊዎች "ኦሮምያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ስለሆነም የኤርትራ ዓይነት መፍተሔ ይደረግላት" ስለሚሉ፣ አማርኛ መናገር እንደ መጥፎ ነገር ስለሚያዩት፣ አፋን ኦሮሞን ከግእዝ ይልቅ በላቲን መጻፍ ስለሚፈልጉ፣ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ተነጥለው የኦሮሞ ብቻ ዓመታዊ የኳስ ጨዋታ በማድረጋቸው፡ ቢያንስ ቢያንስ የስነልቦናዊ መገንጠል አካሂደዋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሑፎቼ እንዳቀረብኩት ኢትዮጵያ ያለ ኦሮሞ ትርጉም የሌላት የፖለቲካ አካል ነው የምትሆነው። ኦሮሞዎች ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ማን ነው ኢትዮጵያዊ የሚሆነው? በእርግጥ የኦሮሞ ብሔር መብት ያለንዳች ገደብ መከበርና መተግበር አለበት፣ ኦነግም እንደሆነ ከሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ድርድርና ውይይት እንድያደርግ መጋበዝ ወቅታዊና ታሪካዊ ይመስለኛል። ከኦነግና ደጋፊዎቻቸው ባሻገር

ግን በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች የኦሮሞ ሕዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያውነታቸው ግን የሚኮሩ ናቸው። እንደያውም፡ ኦሮሞ የኢትዮጵያ አከርካሪ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ። ከነዚሁ አንዱ አቶ ኢብሳ ገዳ ናቸው፣ እንዲህም ይላሉ፦ "እኔ የኦነግ አባል ነኝ...የመገንጠሉን ጥያቄ ያነሳነው ጭቆና ነው። ጭቆና ከተወገደ የኦሮሞ ሕዝብ ከመገንጠል ጋር ጉዳይ አይኖረውም። በመሰረቱ ኦሮሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ግንድ እንጂ ቅርንጫፍ አይደለም። ስለሆነም ግንድ አይገነጠልም።...ኢትዮጵያውነትም እኔ በግሌ ጥላቻ የለኝም። ኢትዮጵያውነት ወንጀል አይደለም። ገዥዎች በዜጎች መሃል 'የበለጠ ኢትዮጵያዊ' የሚባል ልዩነት ስለፈጠሩ የመጣ ችግር ነው። በመሰረቱ ኢትዮጵያ ማለት የተቃጠለ ፊት ወይም ጥቁር ማለት ከሆነ እኛ የበለጠ ኢትዮጵያዊ ነን"[3]

ማን ነው ኢትዮጵያዊ? በ 'ሀ' ና 'ለ' ስብስቦች ዙርያ የተደራጁት ትምክህተኞች ወይስ የአቶ ኢብሳ ዓይነት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን? የዚሁ መልስ ለአንባቢ ትቼ ወደ ሦስተኛው የትንታኔው ክፍል ልሻገር።

3. የምሁራኑና ሊሂቃኑ ታሪካዊ ሓላፊነትና ሚና፦ በታሪክ እንደታየውና ከአጠቃላይ የሰው ተመክሮ እንደተገነዘብነው ሁሉ በኅብረተሰባዊ ለውጥና አገር ግንባታ ምሁራኑና ሊሂቃኑ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። መሰረታዊ ለውጥ፡ ዕድገትና ብልጽግና እንዲኖር ከተፈለገ ምሁራን በብዙ ረገድ መሳተፍ አለባቸው። ያለ ምሁራንና ሞያተኛ ለውጥና ዕድገት ወይም ስኬታማ ልማት ይኖራል ማለት ደግሞ ዘበት ነው። ምሁር ሲባል ታድያ ሁሉም ጨዋና ጻድቅ ማለት አይደለም። አንዳንዱ ምሁር ለሕዝቡ የሚቆረቆር፡ አገር ወዳድና አርበኛ ሲሆን፣ ሌላው ምሁር ለሆዱ የሚገዛ ነጻ አመለካከት የሌለውና አመቺ ሁኔታ ከገጠመውም በሙስና የሚዘፈቅ ነው። ከነዚሁ ሁለት እጅግ በጣም የተራራቁ ምሁራን ከመሃል የሰፈረና በፖለቲካዊ አብዮት ሂደት ላይ ያንቀላፋ ዝምተኛ ምሁርም አለ። በረዥሙ ያገር ግንባታ ጉዞ ላይ አስተዋጽኦ ስለማያደርግ ደግሞ የጋን መብራት ሆኖ ይቀራል።

በአርበኛው ምሁርና በአድርባይ ምሁር ሁልጊዜ የደም መፋሰስ ጦርነት እንኳ ባይካሄድ የተራዘመ ፍልምያና ግጭት ግን አይቀሬ ነው። የፈለገውን መንገድ ቢቀየስ፣ በድርድርና በማግባባት ለማቅረብ ቢሞከርም፡ አድር ባዩ ሐሳቡን አይቀይርም። አርበኛው ታድያ ከንቱ ጥረት ከማድረግ ይልቅ በተለመው የትግል መንገድ ቢራመድ የበለጠ ውጤት ያገኛል፣ በጉዞውም ላይ በርካታ ጨዋ ኢትዮጵያውያን ያገኛል፣ በተባበረ ክንድና በረቀቀ ፖለቲካዊ ስልት ደግሞ ግቡን ለመምታት አስፈላጊውን ዝግጅትና ተግባሮችን ያከናውናል፣ ተከታዮቹን ያነቃል፡ ያደራጃል፣ አብዮቱና የሃገር ግንባታው ዘለቄታ እንዲኖሮው ያደርጋል። አርበኛው ምሁር ደከመኝ ታከተኝ አይልም፣ ብልህና ቆራጥም ነው። የ 'ሀ' ና 'ለ' ስብስቦች መመጻደቅ፡ አሉባልታና ዛቻ አይበግረውም። ስሙ-ጥሩ ኢትዮጵያዊ ነውና።

ለማጠቃለል ያህል፣ አሁን የተፈጠረው የጎጥ ጠባብ አመለካከት ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስብን በቅጡ ተገንዝበን ሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በያለንበት ተሰባስበን ትምህርትና ውይይት መድረኮች በመክፈት ዘለቄታ ያለው ፈውስ የምንፈጥርበት መንገድ መቀየስ አለብን። ለዚሁ ዓይነት ጉባኤ ወይም መድረክ ቅድመ-ሁኔታ ደግሞ ሁለት ነገሮችን የሚጠይቅ ይሆናል፦ 1) ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከአንድ እናት ማህጸን እንደ ወጡ በማሳብ መፈቃቀር፡ መከባበርና መተዛዘን አለባቸው፣ ጥቃቅን ልዩነቶችን መጥቆ በማለፍ ደግሞ በኢትዮጵያ ሃገራዊ ጥቅም ላይ እጅና ጓንቲ ሆነው መስራት አለባቸው፣ 2) ንቃተ ኅሊናቸው የላቀ ኢትዮጵያውያንና የፖለቲካ ድርጅቶች የአንድ ብሔር ተወላጆች ባጠቃላይ እንዳያወግዙና እንዳያጥላሉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ሓቁን ፍርጥርጥ አድርገው በማውጣት ደግሞ ሕዝቡን ማስተማር አለባቸው።

እኔ በበኩሌ፡ በመጠኑም ቢሆን፡ የተቻለኝን ያህል ጽሑፎች በማቅረብ የተዛቡ አመለካከቶችን እንዲታረሙ በተደጋጋሚ ሓሳብ አቅርብያለሁ። የዛሬ አራት ዓመት ለምሳሌ <u>ለኢትዮጵያ የሚበጅ የፖለቲካ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ታሪካዊ ሓላፊነት ነው</u> በሚል ርእስ ጻፍኩት ለአሁኑ ድርሰት አግባቢነት ያለው በዚህ መልክ አቅርቤው ነበር፦

“አንድን ብሔር ወይም የአንድን ብሔር አባላት በደፈናው ማውገዝና መርገም የተሳሳተ ርእዮተዓለም ብቻ ሳይሆን የዝቅተኛ ንቃተ ህሊና አመለካከት ነጸብራቅም ነው። ከዚሁ አጉል ንቃተ ህሊና ጋር የተያያዘ የአካኪ ዘራፍ ፖለቲካ በተደጋጋሚ ሲያስተጋባ ሰምተነዋል። አንድን ሕዝብ ወይም ጎሳ በጭፍንና በደፈና የመጥላት ዝንባሌ ምንጩና ሂደቱ በስነ-ልቦናዊ ትንተና ማየቱ ትንሽ ብያዳግትም በግብር ግን ብዙ ጊዜ ሲተረጎም አይተነዋል። ለውይይት ይመች ዘንድ እስቲ አንዳንድ ታሪካዊ ምሳሌዎች እንጥቀስ፦

ከአፄ ምንሊክ እስከ አፄ ኃይለስላሴ ብሎም እስከ ደርግ የነበሩትን ስርዓቶች ሲተነተኑ አንዳንድ ንቃተ ህሊናቸው ዝቅተኛ የሆነውን የትግራይ፡ የኦሮሞ ወዘተ ጠቅላላ ያማራን ህዝብ የሚያወግዙበት ግዜ ነበር። የላቀ ንቃተ ህሊና ያላቸው የትግራይ፡ የኦሮሞ ወዘተ ተወላጆች ግን ሰፊውን ያማራ ህዝብ በቸነፈርና በድህነት ይሰቃይ እንደነበር ከመገንዘባቸውም በላይ ስለዚሁ ጉዳይ (የመደብ ቅራኔ በተመለከተ) ሰፊ ቅስቀሴ አካሂደዋል፡ አስትምረዋል፡ ታግለዋል። ሃቁን ከተናገርን ደግሞ ባፄ ምንሊክና ባፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ያማራ ህዝብ ያገኘው ንጥረነገራዊ ጥቅም የለም፣ ስነ-ልቦናዊ ኩራትና ስሜት ካልሆነ በስተቀረ። በርግጥ ከገዢው መደብ ጋር የተቆራኙ መኳንንት፡ ባለስልጣናት፡ ትላልቅ ባለጸጎችና ነፍጠኞች በድሮው ስርዓት ተጠቃሚዎችና በዝባዦች ነበሩ። ሰፊው ያማራ ህዝብ ግን ድሃና ምዝብር ለመኖሩ የሚያጠያይቅ አይደለም። የዚሁ ሓቅ ምስክር በመንዝና ተጉለት፡ በጎጃምና በጎንደር የነበረውን አሰቃቂ ድህነትን ነው።”[4]

የመንግሥት ባለስልጣናት በፈጸሙት ወንጀል አንድን ሕዝብ ወንጀለኛ ነው ብሎ መከራከር በታሪክ ሰነድ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ ያልታየ አስተሳሰብና ርትዑነትን ያንጸባርቃል። ምናልባት ለእንዲህ ዓይነት አስተያየት ለሚያራምዱ ግለሰቦችና ስብስቦች ይከሰትላቸው ዘንድ አቶ ተስፋዬ ገብረአብ በመጽሓፋቸው ያተቱትን ላቅርብላችሁ፡-

"ህጋዊ ሽፋን በለበሰው በዚሁ ዘረፋ የትግራይ ህዝብ ተጠቃሚ አለመሆኑን ለሌላው ዜጋ ማሳመን አስቸጋሪ ቢሆንም፡ እውነታው ግን እንድያ ነው። በኢትዮጵያውነቱ ፍጹም ጥርጣሬ እንደሌለው የሚታመነው የትግራይ ህዝብ ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ቂም ቋጥሮ ጥቂት ፋብሪካዎችን በማግኘት ዘላቂ ጥቅም ሊያገኝ እንደማይችል፡ ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ተጋግዞ ማደግን እንደሚመርጥ፣ ይህንንም ፍላጎቱን የኛ ዘመን መሪዎች አሻግረው ሊያዩ አለመቻላቸውን ብዙዎች የትግራይ ምሁራን የሚያስቆጭ ሆኖአል።"[5]

## ዋቢ ጽሑፎች


1. ብ/ጀነራል ኃይለ መለሰ፡ <u>የትግራይ ሕዝብ የሚያሳየው ሁኔታ፣ ይሁንታ? ወይስ መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመ ዝምታ?</u> ሚያዝያ 2001፣ ገጽ 27
2. አምሃ ዳኘው፡ <u>በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍና ትብብር ጥያቄ</u> ገጽ 8
3. ተስፋዬ ገብረአብ፡ <u>የጋዜጠኛው ማስታወሻ</u> Sunnyside Publishers, South Africa, 2008, pp. 325-326
4. ገላውዴዎስ ኣርኣያ፡ <u>ለኢትዮጵያ የሚበጅ የፖለቲካ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ታሪካዊ ሓለፊነት ነው</u> www.africanidea.org/Doc5.pdf July 2, 2005
5. ተስፋዬ ገብረአብ <u>የጋዜጠኛው ማስታወሻ</u> ገጽ 181


All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc. 2009